# ዘላቂ ልማትና መልካም አስተዳደር!

## ክፍል ሁለትና የመጨረሻ

## በሽር ሁሴን 12-19-14

ለዴሞክራሲው ግንባታ እውን መሆንና ላሳየው የማይናወጥ ቁርጠኝነት “አበጀህ” ሊባል ይገባል እንጂ፣ ያለ አንዳች ማስረጃ በመንግስትና በተቋሙ ላይ በደፈና ጥላቻ እየታገዙ የውርጅብኝ መዓት ማውረድ ተገቢ አይመስለኝም። ክንዋኔዎችን በአንክሮና በሰከነ አዕምሮ ከሚያይ ፓርቲ የሚጠበቅም አይደለም።

የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የዜጎችን አስተዳደራዊ በደል ተገቢው ምላሽ እንዲያገኝ በርካታ ስራዎችን በማከናወን ውጤት እያስመዘገበ መሆኑ እየታወቀ፣ በስሜት ብቻ እየተገፋፉ የተቋሙን ስም ለማጥፋት መሯሯጥ እንዲሁም የመንግስት በዘርፉ እያደረገ ያለውን ጥረት በፀረ-ዴሞክራሲያዊነት ታፍኖ ላለመቀበልና ለማጣጣል መሞከር “ዓይናችሁን ጨፍኑና ላሞኛችሁ” ዓይነት በመሆኑ በየትኛውም መስፈርት ተቀባይነት የለውም። ራሱ ተቃዋሚ ነኝ ባዩ አካልም ቢሆን አመለካከቱ ገንቢና ዴሞክራሲያዊ ባለመሆኑ በእንዲህ ዓይነቱ ጭፍን እሳቤ ጉዞው ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደቱ አሜኬላ እሾህ መሆኑ አይቀርም።

መልካም አስተዳደር የሚታሰበው ስርዓቱ ተግባሩን ለማከናወን ካለው በጎ ምልከታ አኳያ መሆኑ እርግጥ ነው። ታዲያ የሀገራችን ፖለቲካዊ ስርዓትም መልካም አስተዳደርን በሂደት ለመፈፀም ቁርጠኝነት ያለው ብቻ ሳይሆን፣ መልካምና የተመቻቸ ምህዳር ጭምርም የነገሰበት ነው። ለምን ቢባል፣ ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ስልጣን የህዝብና የህዝብ ብቻ መሆኑን በግልፅ በማስቀመጡ ነው። ስልጣን የተገለጋዩ ህዝብ መሆኑ ደግሞ፣ ለመልካም አስተዳደር እመርታ የራሱ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የሚካድ አይደለም።

ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እንደሚገነዘበው፣ መልካም አስተዳደር የተግባር እንጂ የንድፈ-ሐሳብ ጉዳይ አይደለም። ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት

ተግባሩ ከዜጎች የዕለት ተዕለት የኑሮ ሁኔታ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ በመሆኑ፣ በአተገባበሩ ላይ የስልጣኑ ባለቤት የሆነው ህዝብ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆን አለበት። ህዝቡ በህገ-መንግሰቱ የተጎናፀፈውን ስልጣን በአግባቡ እንዲጠቀምበት ዕድል ይፈጥራል።

ታዲያ የሀገራችን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ይህ ሁኔታ እንዲተገበር በርካታ ተግባራትን አከናውኗል። ቀደም ሲል የጠቀስኩት የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም እንዲሁም የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ችግሮችን እየተከተታተሉ በማረም ለመልካም አስተዳደር ግንባታው የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ከተቋቋሙት ገለልተኛ አካላት ውስጥ ለአብነት ያህል የሚጠቀሱ ናቸው።ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ እነዚህ አካላት እንዲቋቋሙ በአዋጅ ከማፅደቅ ጀምሮ፣ ተግባራቸውንም የመልካም አስተዳደር ዕመርታን በሚያረጋግጥ አኳኋን እንዲፈፅሙ እስከ ማድረግ ድረስ አመቺ የሆኑ ሁኔታዎችን ፈጥሯል።

እነዚህ ገለልተኛ አካላት ህዝቡ በህገ-መንግስቱ ላይ የተቀመጡለት መሰረታዊ መብቶቹ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። እስካሁንም ድረስ በርካታ ህዝባዊ ጉዳዮችን በመመልከት የተጣለባቸውን ሃላፊነት በብቃት እየተወጡ ነው—አቅም በፈቀደ መጠን። የመልካም አስተዳደር ስራ በርካታ ዓመታትን የሚጠየቅ ከመሆኑም በላይ፣ሀገራችን ካለባት የማስፈፀም አቅም ውስንነት አኳያም ተያይዞ የሚታይ ነው። ይሁንና በአሁኑ ወቅት ያለው የመልካም አስተተዳደር ትግበራ አፈፃፀም  የአቅም ውስንነትን ተሻግሮ መሻሻል እያሳየ ነው።

ይህ ማለት ግን ፈፅሞ የመልካም አስተዳደር ችግር የለም ማለት አይደለም። በአስቸኳይ መፈታት ያለባቸው ችግሮች በአፋጣኝ መፍትሔ እየተሰጣቸው ነው። ሌሎችም እየታዩ በሂደት ምላሽ ያገኛሉ። የጊዜ ጉዳይ እንጂ ማንኛውም የመልካም አስተዳደር ችግር በሂደት የሚስተካከል ነው። ሆኖም እንደ ተቃዋሚዎቹ ሁሉንም ነገር የመደፍጠጥ አባዜ ‘ምንም አልተሰራም’ የሚል ዲስኩር ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም በተጨባጭ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት ህያው አብነቶች ናቸውና።

ተቃዋሚ ተብዬዎች በተለያዩ ህጋዊ አግባቦች አለመሟላት ምክንያት ምላሽ ያልተሰጠውን አንድ ነጠላ ጉዳይ በመምዘዝ እንዲሁም "የአይጥ ምስክር ድንቢጥ" እንዲሉ እነ ሂዩማን ራይትስ ዎችን የመሳሰሉ በክቡሩ የሰው ልጅ ስም የሚነግዱ አክራሪ ኒዩ-ሊበራሌችን በመጥቀስ የተቋማቱን መልካም የስራ ውጤት ገደል ለመክተት ይጥራሉ። ይህ ደግሞ ዕውነታውን ለሚያውቀው ህዝብ አሁንም ቢሆን እነዚህ ወገኖች ካለፈው ድርጊታቸው አለመማራቸውን የሚያረጋግጥ ሃቅ ነው። በተቃውሞው ጎራ የተሰለፉ ተቃዋሚዎች አንዳንዴም እንኳን ቢሆን የተከናወኑ ተግባራትን ዓይናቸውን ገልጠው ቢመለከቱ መልካም ይመስለኛል። የተቃዋሚነት ወግና ባህል ይኸው ነውና። በመሆኑም የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚ የሆነውና የስልጣን ባለቤትነቱን ያረጋገጠው ህዘብ፣ ስልጣኑ በእርሱ እጅ መሆኑን ዛሬም ቢሆን ነገ አምነው መቀበል ይኖርባቸዋል።

እነዚህ ወገኖች የመልካም አስተዳደር አስፈፃሚ የሆኑትን የሲቪል ሰርቪሱን አወቃቀርና አሰራር እንዲሁም የዳኝነት ስርዓቱን ለመኮነንም ተወዳዳሪ አልተገኘላቸውም፣ ያለ አንዳች የነጠረ ፖሊሲና ስትራቴጂ። ግና በመጀመሪያ ስለ እነዚህ ጉዳዩች በቂ ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል። 'አሁን ያሉበትስ ደረጃ ምንድው?' ብሎ መጠየቅም ያባት ነው። በመያውቁት ጉዳይ ውስጥ ገብቶ መፈትፈት ግምት ላይ የሚጥል አስነዋሪ ተግባር ነው።

በእኛ ሀገር ዕውን በሆነው ባልተማከለው ፌዴራላዊ ስርዓት መሰረት፣ ህዝቡ የፖለቲካ መሪዎቹንና ተወካዩቹን ከቀበሌ እስከ ፌዴራል ደረጃ ድረስ ይሾማል፣ይሽራል። ህዝቡ በምርጫ ካርዱ አማኝነት በቀጥታ የስልጣን ባለቤት የሆነበት ይህ አሰራር በስርዓቱ ውሰጥ ወሳኝ ሚና ቢኖረውም፣ በህዝቡ በቀጥታ የማይመረጡና ሊመረጡ የማይችሉ አካላት መኖራቸው አይቀርም። በዚህ የአሰራር ማዕቀፍ ውስጥ የሚጠቀሱት ስራ አስፈፃሚው ሲቪል ሰርቪሱና የዳኝነት አካላት ናቸው።

እነዚህ አካላት ለመልካም አስተዳደር አተገባበር ያላቸው የማይተካ ሚና

ስለሚታወቅም፤ እንደ ማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ሀገር በምክር ቤቶች የሚሾሙ ወይም ለምክር ቤቶቹ ተጠሪ ይሆናሉ። ሆኖም ግን የየራሳቸው ነፃነት ያላቸው አካላት መሆናቸውን መዘንጋት አያስፈልግም። በመሆኑም ተቃዋሚዎቹ ስራ አስፈፃሚውና ሲቪል ሰርቪሱ ማንም እንዳሻው የሚፈነጭባቸው አካላት አለመሆናቸውን ማወቅ ይኖርባቸዋል። ከዚህ ይልቅ ህዝቡና የህዝቡ ተወካዮች በዴሞክራሲያዊ ሁኔታ መክረው ያፀደቋቸውን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ህጎች በተሟላ ሁኔታ የሚያስፈፅሙ እንዲሁም ለሁሉም ዜጋ ያለ አድልኦ ፈጣን አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸውን ተቃዋሚዎቹ እየመረራቸውም ቢሆን መቀበል አለባቸው። ምክንያቱም እነዚህ አካላት ይህን በማድረጋቸው የህዝቡ ሉዓላዊነት መሳሪያዎች፣ አገልጋዩችና የመልካም አስተዳደር ፈፃሚዎች ከሆኑ በርካታ ዓመታትን በማስቆጠራቸው ነው።

የሲቪል ሰርቪስ ስርዓቱ የተጠቃሚው መብትና ጥቅም እንዳየሸራረፍ እንዲሁም ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን በርካታ ተግባባራትን አከናውኗል። ይህ ተግባርም መንግስት በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን መተኪያ የሌለው ድርጊት መሆኑን እንደሚያምንና በቁርጠኝነት ለመተግበርም በሃላፊነት ስሜት መንቀሳቀሱን የሚያመላክት ነው።

ከዳኝነት ስርዓቱ ጋር በተያያዘም፤ህዝቡ በተወካዩቹ አማካኝነት ያፀደቀውን ህገ-መንግስትና ይወክሉኛል ባላቸው አካላት አማካኝነት የሚወጡ ህጎችን በትክክል መተርጎሙ፣ በዚህ መሰረትም አቅም በፈቀደ መጠን ለባለ ጉዳዩ ፈጣንና ትክክለኛ ፍትህን ያለ አንዳች አድልኦ ስር በመስደድ ላይ ነው።

ታዲያ እዚህ ላይ ከሀገራችን ለጋ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት አኳያ ሲቪል ሰርቪሱም ይሁን የዳኝነት ስርዓቱ ፍፁማዊ ደረጃ ላይ ደርሰዋል እያልኩ አለመሆኔን ውድ አንባቢዎቼ እንዲገነዘቡልኝ እፈልጋለሁ። ዴሞክራሲው ገና ጅምር በመሆኑ ካለፉት ስርዓቶች የወረስናቸው የተለያዩ አመለካከቶች እንቅፋት መፍጠራቸው አይቀሬ ነው። ይሁንና መንግስት ይህን ሁኔታ ለመቅረፍ ችግሮቹን በአፋጣኝ ለመፍታት በርካታ እርምጃዎችን ወስዷል።

የሰለጠነ የሰው ሃይልን በመፍጠርና ስርዓቱ የሚፈልገውን የስራ አስፈፃሚና የህግ ተርጓሚ አካላትን ዕውን ለማድረግ የማስፈፀም አቅምን በመገንባት ረገድ የወሰዳቸው ወሳኝ እርምጃዎች ተጠቃሽ ናቸው። የሰው ሃይልን በተግባር ሂደት የማብቃት፣ አሰራርና አደረጃጀትን ለማሻሻል የሚያስችል የሲቪል ሰርቪስና የፍትህ አስተዳደር ማሻሻያ ተቀርፆም ወደ ተግባር በመግባት ከፍተኛ ውጤት ተገኝቶበታል። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ሊያሰራ የሚችልና ወደፊት የሚጎለብት የማስፈፀም አቅምን በሲቪል ሰርቪሱና በዳኝነት ስርዓቱ ውስጥ ለመገንባት ተችሏል።

በጥቅሉ ላይ የጠቀስኳቸውና ሌሎች የመልካም አስተዳደር ተግባራት ተከናውነው ውጤት ተገኝቶባቸዋል።ይህን ዕውን ለማድረግም መንግስት በየደረጃው ተጨባጭ እርምጃዎችን ወስዷል። እጅግ በርካታና የተወሳሰቡ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ካለፉት ስርዓቶች የተረከበ ቢሆንም፣ ተግባሩ ምንም እንኳን ጊዜንና ጥረትን ቢጠይቅም፣  ችግሮቹን ለማስወገድ በየደረጃው ተገቢ ናቸው ብሎ ያነባቸውን እርምጃዎ ወስዷል፤ በመውሰድ ላይም ይገኛል።

የኪራይ ሰብሳቢነት ፖሊቲካዊ-ኢኮኖሞሚ አስተሳሰብን በልማታዊነት ለመተካት እያደረገ ያለው ጥረትም ከወዲሁ ተስፋ ሰጪ የሆኑ ውጤቶችን ማስመዝገብ ጀምሯል፤ ወደፊትም ተጠናክሮ ይቀጥላል። እነዚህ ዕውነታዎች መልካም አስተዳደር በሂደት ስር የሚሰድ እንዲሁም እያበበ የሚጎመራ መሆኑን የሚያላክቱ እንጂ፤ በተቃውሞው ጎራ የተሳሳተው "የሱሪ ባንገት" ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ብሂል ገቢራዊ ሊሆን እንደማይችል የሚያረጋግጡ ናቸው። ዳሩ ግን ተቃዋሚዎች ያሻቸውን ቢሉም፤ በሀገራችን እየተገነባ ያለው የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ስርዓት በጊዜ ዑደት ውሰጥ አሁን ካለው ዕመርታ በላይ እየገመራ መሄዱ አይቀሬ ነው።

መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እየተከናወኑ ባሉ  ሥራዎች ላይ የህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ከማረጋገጥ አንጻር የተወደው እርምጃ በገጠርም ሆነ በከተማ የላቀ ፋይዳ

እንዳለው ይታመናል፡፡ ፍትህና መልካም አስተዳደር ስፋትና ጥልቀት እያገኘ የሚጠናከረውና ለቀጣይነቱ ዋስትና የሚያገኘው አሳታፊና ፍትሐዊ የሆነ ፈጣን ልማት በማምጣት ብቻ እንደሆነ እሙን ነው፡፡

ፈጣን፣ ፍትሐዊና ቀጣይ ልማትን ለማረጋገጥ መልካም አስተዳደር ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ እንዳለው ይታወቃል። ለልማት የበላይነት ደግሞ ኪራይሰብሳቢነትን መድፈቅ የግድ ይላል። ፍትሃዊ ልማትና መልካም አስተዳደርን አስተሳስሮ ማስኬድ ብቸኛው የልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መንገድ በመሆኑ ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት መልካም አስተዳደርን ከልማት ጋር አስተሳስሮ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ማቅረብ ሌላ ለፍትህና ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ወሳኝ ነው።

የተለያዩ አገልግሎቶች፣ የልማትና የአስተዳደር ሥራዎች ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለነዋሪዎች የሚቀርቡበትን የአሰራር ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ ይህንን መርህ በተግባር ለመተርጎም የአገልግሎት ሰጭና ተቀባይ መብትና ግዴታን በግልጽ መለየትና ማሳወቅና ሥራዎቹን ለመፈጸም የሚያስችል የአደረጃጀትና የሰው ኃይል አቅም መፍጠርን፣ አማራጭና ዘመናዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎችን መጠቀም ማዕከል ያደረ እንቅስቃሴ ይደረጋል፡፡ ይህንን በዋናነት ሕብረተሰቡ ሊከታተለውና በባለቤትነት ሊይዘው የግድ ይላል።

መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና ኪራይሰብሳቢነትን በልማታዊነት ለመተካት ቀልጣፋና ፍትሀዊ አገልግሎት መስጠት የሚያስችለው አደረጃጀት አለመፍጠሩ ሌላው የዘርፉ ማነቆ ነው። ፍትህና መልካም አስተዳደር ማረጋገጥ ከተቻለ ሕዝቡ በምክንያት የተመሰረተ ድጋፍና ተሳትፎ ለማድረግ እድል ይኖረዋል። ከዚህም ባሻገር ለዴሞክራሲ ስርዓት መጠናከር፣ ለአስተማማኝ ሰላም መስፈን እንዲሁም ለህግ በላይነት መረጋገጥ አወንታዊ ተራ ይኖረዋል።

ፍትህንና መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ በየደረጃው ያሉ አመራሮችን ሙያተኞችን አቅም በቀጣይነት ማሳደግ፣ ስለሚሰጧቸው አገልግሎቶችና

ስለሚያከናውኗቸው የልማት ሥራዎች ግልጽ ግቦችን ማስቀመጥ፤ ለህዝቡም በየደረጃው ግልጽ ማድረግ ያሻል። ፍትህንና መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ ፈርጀ ብዙ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም የተፈለገውን ያህል ውጤት ማምጣት ቀላል አልሆነም። ዘርፉ ለበርካታ ዓመታት የነበሩበትን ችግሮች ሙሉ በሙሉ ለመቅረፍ የሚደረገው ጥረት መጓተት ታይቶበታል።

እነዚህ ለዘመናት የዘለቁ የፍትህና የመልካም አስተዳደር ተግዳሮቶችን ለመሻገር አሁንም ጥረቱ ቀጥሏል። የፍትህ ማሻሻያ ተነድፎ ስራ ላይ ውሏል። ማሻሻያው በዘርፉ የሚታዩ መሰረታዊ ማነቆዎችን በመለየት ችግሮቹ ለመፍታት የሚያስችል እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል። ፍትህንና መልካም አስተዳደርን በዘላቂነት ማረጋገጥ የሚቻለው ፈጣንና ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ ሕብረተሰቡ በየደረጃው ተጠቃሚ መሆን ሲችል ነው።

ሕዝቦቿን መመገብ ያልቻለችና በድህነት የተዘፈቀች አገር ፍትሃዊነትና መልካም አስተዳደርን ማስፈን አትችልም። ዜጎች ፍትሃዊ የሃብተ ክፍፍል፣ ፍትሃዊ የትምህርትና የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ማግኘት፣ ተመጣጣኝ የመሰረተ ልማት ተጠቃሚ መሆን ካልቻሉ መልካም አስተዳር እውን ሆኗል ማለት ያዳግታል።

ልማትን ማረጋገጥ ለፍትህና መልካም አስተዳደር መረጋገጥ የበኩሉ አወንታዊ ሚና እንዳለው ሁሉ ፍትህንና መልካም አስተዳደርን እያረጋገጡ መሄድም ለልማቱ መፋጠን ቀላል የማይባል አወንታዊ ድርሻ ይኖረዋል። ሁለቱ ዓበይት ነገሮች እርስ በርሳቸው ተመጋጋቢ ናቸው።

ሰፊ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴ ማዕከል በሆነችው ኢትዮጵያ እየተመዘገበ ያለው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት የሚያበረታታ ነው። የፍትህ ሴክተሩ በአገሪቱ ልማት የሚኖረውን በጎ ሚና እንዲወጣ በማድረግ ረገድ እጥረት ታይቷል። በዚህ የተነሳ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ለማጠናከር በሚደረገው ጥረት ዘርፉ ያበረከተው አስተዋጽኦ የቀጨጨ ነበር ማለት ይቻላል።

ልማታዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚን ለማረጋገጥ እየተደረገ ያለው ጥረት የፍትህ ስርዓቱን በማሻሻልና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በገጠር መሰረቱ የተናደው የኪራይሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ በከተማም መደርመስ እየጀመረ ይገኛል። ይህንን እየደረመሱ ልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚን ለማስረጽ እየተደረገ ያለው ጥረት በየደረጃው  ቀላል የማይባል ርብርብ እየተደረገበት ይገኛል።